አንተ ልጅ ሆይ! ቢስሚላህ በል! በቀኝህ ብላ፣ ፊትህ ካለውም ብላ!

ከዑመር ቢን አቢ ሰለማህ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "በአላህ
መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጎጆ ውስጥ የምኖር ህፃን ልጅ ነበርኩ። በማዕዱ ላይም እጄ ትሽከረከር ነበር። የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለኔ እንዲህ አሉኝ ' አንተ ልጅ ሆይ! ቢስሚላህ በል! በቀኝህ ብላ፣ ፊትህ ካለውም ብላ!' ከዚያን ጊዜ በኋላ ከዚህ የአበላል ስርአት አልተወገድኩም።" [ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ዑመር ቢን አቢ ሰለማህ (ረዲየላሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና የነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ባለቤት የሆነችው የኡሙ ሰለማህ ልጅ ነው። ያደገውም በሳቸው እነፃና እንክብካቤ ስር ነበር። በሚበላበት ወቅት ምግብ ለማንሳት እጁን በእቃው ዙሪያ ያዘዋውር ነበር። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሶስት የአመጋገብ ስርአቶችን አስተማሩት: የመጀመሪያው: መብላት ሲጀምር "ቢስሚላሂ" ማለት ነው። ሁለተኛው: በቀኝ መብላት ነው። ሶስተኛው: ለርሱ ቅርብ በሆነ ምግብ በኩል መመገብ ነው።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/58120